# መንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 16/2013

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**አንቀፅ 1.** **አውጪው ባለስልጣን**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁ. 1162/2011 አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል።

**አንቀጽ 2.** **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"ከመንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ መመሪያ ቁጥር 16/2013"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 3.** **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፤

1. **"አዋጅ"** ማለት የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ማለት ነው።

2. **"የአካል ጉዳተኛ"** ማለት በዘላቂ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ምክንያት ለጉዳት ተጋላጭ የሆነና የእኩል እድል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ነው።

3. **"የመንግስት የገንዘብ ወይም የፋይናንስ ድጋፍ"** ማለት በአዋጁ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲዎች ህጋዊ ስራቸውን ለማከናወንና ሃላፊነታቸውን ለመወጣት እንዲችሉ መንግስት በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና/ወይም በአገልግሎት መልክ የሚሠጠው ድጋፍ ነው።

4. **"የመራጮች ድምጽ"** ማለት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ለክልል ምክር ቤቶች ላቀረባቸው እጩዎች ያገኘው ተቀባይነት ያገኘ ጠቅላላ የመራጮች ድምጽ ነው።

5. **"ምርጫ"** ማለት ጠቅላላ ምርጫ ነው

6. **"ጠቅላላ ምርጫ"** ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው።

7. **“ኦዲተር”** ማለት የሞያ ብቃቱ አግባብነት ባለው አካል የተረጋገጠ ሆኖ በማናቸውም ሁኔታ የጥቅም ግጭት ሊያመጣ የሚችል ግንኙነት ከፓለቲካ ፓርቲውም ሆነ ከአመራሩ ጋር ግኑኝነት የሌለው በፖለቲካ ፓርቲ የሚሾም ሰው ነው።

8. **“የሥራ ዘመን”** ማለት በሕገ መንግስቱና በምርጫ ህጉ መሠረት የህዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ የሚካሄድበት የአምስት ዓመት የሥራ ጊዜ ነው።

9. **“የፖለቲካ ፓርቲ ሃላፊዎች”** ማለት እንደሁኔታው የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ የሥራ አስፈጻሚ አባላት፣ ወይም በተመሳሳይ የሥልጣን ደረጃ ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ናቸው።

10. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

11. በምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1133/2011 እና የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ላይ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ።

**አንቀጽ 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ህጋዊ እውቅና ተሰጥቷቸው በፌዴራል ወይም በክልሎች በሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 5. <u>የጾታ አገላለፅ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በአንዱ ፆታ የተደነገገው ሌላኛውንም ያካትታል።

**አንቀጽ 6. <u>አላማ</u>**

የዚህ መመሪያ ዓላማ መንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ የሚከፋፈልበት መስፈርት ወይም ቀመር እንዲሁም አጠቃቀም እና አስተዳደር በተመለከተ ግልጽ አሰራር በመዘርጋት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዘለቄታዊ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል ነው።

**አንቀጽ 7. <u>የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚከፋፈልበት መርህ</u>**

1. ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የመንግሥት ድጋፍ በአዋጁ ላይ በተደነገገው መሠረት በፍትሃዊነት እና ያለ አድልዎ መፈጸም አለበት።

2. የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ተግባር ማዋላቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የግልጽነትና የተጠያቂነት ስርዓት መዘርጋት አለባቸው።

3. በቦርዱ በተለየ ሁኔታ የተወሰነ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ ቀድሞ ለተካሄደ የምርጫ ወጪ መሸፈኛ ሊጠየቅ አይችልም።

4. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በመንግስት በሚሰጥ ማንኛውንም የፋይናንስ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆን አይገደድም።

5. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ሂሳቡን በሕግ መሠረት ማንቀሳቀስ አለበት።ከተፈቀደለት ውጪ ወጪ ማድረግ አይችልም።

## ምዕራፍ ሁለት

## <u>የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ምንጭ፣ ዓይነት እና ድጋፉ ለፓርቲዎች የሚከፋፈልበት መስፈርት</u>

### አንቀጽ 8. <u>ከመንግስት ስለሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ምንጭ</u>

መንግስት በአዋጁ አንቀጽ 101 መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ፡-

1. ከመንግስት የሚመደብ፣

2. ከውጭ፣ ከሀገር ውስጥ ወይም ከሌላ ከማንኛውም አካል ከሚገኝ ድጋፍ ወይም እርዳታ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 9. <u>ስለድጋፍ ዓይነት</u>

በአዋጁ አንቀጽ 100 መሠረት መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ እንደ ሁኔታው፡-

1. በጥሬ ገንዘብ
2. በቁሳቁስ እና
3. በአገልግሎት ሊሆን ይችላል።

### አንቀጽ 10. <u>ፓርቲዎች ከመንግሥት የሚያገኙትን ድጋፍ ለታለመለት ተግባር ብቻ ስለመጠቀማቸው</u>

1) በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚያገኙትን የገንዘብ ድጋፍ ህጋዊ ስራቸውን እና ሃላፊነታቸውን ለመወጣት መጠቀም አለባቸው፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚያገኙትን ገንዘብ ለሚከተሉት አላማዎች መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ) የመራጩ ህዝብ የፖለቲካ ግንዛቤና እውቀት እንዲዳብር ለማድረግ፣

ለ) ዜጎች በአገራቸው የፖለቲካ ጉዳዮች የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለማድረግ፣

ሐ) የፓርቲውን አላማ ለህዝቡ ለማስተዋወቅ፣

መ) የምረጡኝ ቅስቀሳ ለማድረግ፣

ሠ) ፓርቲው በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 እና ቦርዱ ባወጣቸው መመሪያዎች የተጣሉበትን የስነ ምግባር ግዴታዎች እንዲሁም አባላትና ደጋፊዎቹን የምርጫው ሰላማዊነት ለማረጋገጥ ያለባቸውን ሀላፊነትና ግዴታ ለማስተማር

ረ) ህብረተሰቡ የምርጫ ሂደቱ ሰላማዊ እንዲሆን መብቱንና ግዴታውን እንዲወጣ ትምህርትና መረጃ ለመስጠት፣

ሰ) የሴቶችና አካል ጉዳተኞችን እጩዎችን የእኩል ዕድል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ፣

ሸ) የፓርቲ እጩዎችን እና ወኪሎቹን ለማሰልጠንና ለማሰማራት እና እነዚህን ለመሳሰሉ ወጪዎች።

3) በመንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ በቦርዱ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተወሰነ በኋላ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች ከግምት በማስገባት በቦርዱ ይከፋፈላል።

## **አንቀጽ 11. <u>በመንግስት የሚሰጥ ድጋፍ መስፈርቶች</u>**

በአዋጁ አንቀጽ 100(2) በተደነገገው መሠረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያገኘው አመታዊ የገንዘብ ድጋፍ የሚወሰነው የሚከተሉትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ነው።

ሀ) ከአባላቱና ደጋፊዎቹ የሚያገኘው ገቢ መጠን፤

ለ) ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የሴት እጩዎች ብዛት፤

ሐ) የፓርቲው የሴቶች ስራ አስፈፃሚ አባላት ብዛት፤

መ) ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የአካል ጉዳተኛ እጩዎች ብዛት፤

ሠ)የፓርቲው የአካል ጉዳተኛ ስራ አስፈፃሚ ብዛት።

## **አንቀጽ 12. <u>በመራጮች ድምጽ ላይ ተመስርቶ የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ</u>**

1) አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለፌደራል እና ለክልል ምክር ቤቶች በተደረጉ ምርጫዎች ለሚያገኘው እያንዳንዱ ተቀባይነት ያገኘ የመራጭ ድምጽ ሃምሳ የብር ሳንቲም የገንዘብ ድጋፍ ከመንግስት ያገኛል። ሆኖም ለመጀመርያዎቹ 5 ሚሊዮን የመራጮች ድምጽ ፓርቲው ለእያንዳንዱ የመራጭ ድምጽ ሰባ አምስት የብር ሳንቲም ያገኛል።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ፓርቲ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተሰጠው ጠቅላላ የመራጮች ድምጽ ያገኘው ከዜሮ ነጥብ ሁለት አምስት (0.25) ከመቶ፣ ወይም ለተወዳደረበት የክልል ምክር ቤት ከዜሮ ነጥብ አምስት (0.5) ከመቶ ያነሰ ከሆነ ይህንን መስፈርት መሰረት በማድረግ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ አያገኝም፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተደነገገው የመቶኛ ቅድመ ሁኔታ አነስተኛ ቁጥር ያለውን ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ለመወከል የተደራጀ ፓርቲን አይመለከትም፡፡ ይህን ፓርቲ በተመለከተ ቦርዱ ፓርቲው የሚወክለውን ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ጠቅላላ ቁጥር ባገናዘበ መልኩ ሊሟላ የሚገባውን የመቶኛ ቅድመ ሁኔታ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 13. <u>ከፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች በሚያገኘው ገቢ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ የገንዘብድጋፍ</u>**

1) አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ ለሚሰበስበው ለእያንዳንዱ አንድ ብር ከመንግስት ሰላሳ የብር ሳንቲም ድጋፍ ያገኛል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ፓርቲ ከአንድ አባሉ ወይም በአዋጁ ለፖለቲካ ፓርቲ ድጋፍ ወይም ስጦታ ማድረግ ካልተከለከለ አንድ ሰው በአመት ከሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው የድጋፍ ቀመር ውስጥ የሚካተተው እስከ ሀምሳ ሺህ ብር ብቻ ያለው ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 14. <u>ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የሴት እጩዎች፣ የሴት አባላት እና ፓርቲው ያለው የሴት አመራር ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ</u>**

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11(ሐ) እና (መ) መሰረት የሚከፋፈለው የገንዘብ መጠን መንግሰት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከሚያደርገው አጠቃላይ የገንዘብ ድጋፍ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ያህሉ ነው፡፡

2) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 11(መ) እና የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ቢኖሩም አንድ ፓርቲ የሴቶች አባላቱ ብዛት ከአምስት (5%) በመቶ በታች ከሆነ መንግስት በሴቶች አባልነት ላይ ተመስርቶ የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ አያገኝም፡፡

3) በዚህ መስፈርት መሰረት እንዲከፋፈል ከተወሰነው ጠቅላላ ገንዘብ ከአምስት በመቶ በላይ የሚኖሩ የሴት አባላትን እንዲሁም የሴት አመራር አባላትን ቁጥር መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ፓርቲ ከመንግሰት የሚደረገው የገንዘብ ድልድል ቀመር የሚወሰንበትን ዝርዝር መስፈርት ቦርዱ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 15. ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የአካል ጉዳተኛ እጩዎች፣ የአካል ጉዳተኛ አባላት እና ፓርቲው ያለው የአካል ጉዳተኛ አመራር ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11(ሠ) እና (ረ) መሰረት የሚከፋፈለው የገንዘብ መጠን መንግሰት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከሚያደርገው አጠቃላይ የገንዘብ ድጋፍ ሰባት በመቶ (7%) ያህሉ ነው። በዚህ መስፈርት መሰረት እንዲከፋፈል ከተወሰነው ጠቅላላ ገንዘብ የአካል ጉዳተኛ አባላትን እንዲሁም አካል ጉዳተኛ አመራር አባላትን ቁጥር መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ፓርቲ ከመንግሰት የሚደረገው የገንዘብ ድልድል ቀመር የሚወሰንበትን ዝርዝር መስፈርት ቦርዱ ይወስናል።

**አንቀጽ 16. በመንግሰት የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ መጠን**

1) በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 12-15 የተመለከቱት የገንዘብ ድጋፎች መጠን በቦርዱ አቅራቢነት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚወስነው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ላይ የተመሰረተ ነው።

2) በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 12-15 መሰረት ሊከፋፈል የሚገባው የገንዘብ መጠን መንግስት ከመደበው የገንዘብ መጠን የሚበልጥ ከሆነ በእያንዳንዱ መስፈርት መሰረት በሚከፋፈለው የገንዘብ መጠን ላይ ምጣኔያዊ ማስተካከያ በማድረግ ድጋፉ ይከፋፈላል።

**አንቀጽ 17. ለ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ለፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግስት የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ መስፈርቶች**

1) የፖለቲካ ፓርቲዎች **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ በመንግስት የሚሰጣቸውን የገንዘብ ድጋፍ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሰረት መጠቀም ይኖርባቸዋል።

2) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ቢኖሩም **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያደርገው የገንዘብ ድጋፍ የሚከፋፈለው በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ በመመስረት ነው።

ሀ) በ**6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ ለሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት የሚሰጥ ገንዘብ፣

ለ) ፓርቲው በሚያቀርባቸው እጩዎች ብዛት፣

ሐ) ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የሴት እጩዎች ብዛት፤

ሠ) የፓርቲው የሴቶች ስራ አስፈፃሚ አባላት ብዛት፤

ረ) ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የአካል ጉዳተኛ እጩዎች ብዛት፤

ሰ) የፓርቲው የአካል ጉዳተኛ ስራ አስፈፃሚ አባላት ብዛት።

3) **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ መንግስት ለግል እጩ ተወዳዳሪዎች የሚያደርገው የገንዘብ ድጋፍ መስፈርት በቦርዱ ይወሰናል።

## አንቀጽ 18. <u>ለ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ለፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግስት የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር</u>

1) በ**6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ ለሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ መጠን መንግስት ለጉዳዩ በሚመድበው ጠቅላላ የገንዘብ መጠን ላይ ተመስርቶ የሚሰላ ሆኖ ክፍፍሉ በሚከተለው ቀመር መሰረት ይሆናል። **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ በመንግስት ከሚመድበው ጠቅላላ የገንዘብ ድጋፍ ውስጥ፤

ሀ) ሃያ አምስት በመቶ (25%) **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ ለሁሉም ፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት የሚከፋፈል፣

ለ) ሃያ አምስት በመቶ (25%) **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ ፓርቲዎች በሚያቀርቧቸው እጩዎች ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚከፋፈል፣

ሐ) ሃያ በመቶ (20%) **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ ፓርቲዎች ለውድድር በሚያቀርቧቸው የሴት እጩዎች ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚከፋፈል፣

መ) አስራ አምስት በመቶ (15%) ፓርቲዎች ባላቸው የሴት ስራ አስፈፃሚ አባላት ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚከፋፈል፣

ሠ) አስራ አምስት በመቶ (15%) **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ ፓርቲዎች ለውድድር በሚያቀርቧቸው አካል ጉዳተኛ እጩዎች ብዛት ላይ ተመስርቶ የሚከፋፈል፣

## 19. <u>ድጋፍን የማከፋፈል ስልጣን</u>

1. ማንኛውም በዚህ መመሪያ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል እጩዎች በመንግስት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ዓይነት እና መጠን በቦርዱ የሚለይና የሚተዳደር ይሆናል። ቦርዱ ለዚህ ተግባር አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይይዛል።

2. ቦርዱ በዚህ መመሪያ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት በመንግስት የሚመደበውን የገንዘብ ድጋፍ ያከፋፍላል፤ ክፍፍሉ የሚከናወንበትን መስፈርትና ቀመር ለተጠቃሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል እጩዎች እንዲያውቁት ያደርጋል።

**አንቀጽ 20. <u>በጥሬ ገንዘብ ስለሚሰጥ ድጋፍ</u>**

1) መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲ በጥሬ ገንዘብ የሚሰጠው ድጋፍ በአገር ውስጥ ባለ ባንክ በተከፈተ የተለየ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት።

2) የፖለቲካ ፓርቲው የተሰጠውን ድጋፍ በተለየ የሂሳብ መዝገብ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መያዝ አለበት፤ በፋይናንስ ህግ መሠረት በበጀት ዓመቱ ከመንግሥት የተሰጠውን የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡን ለምን ተግባር እንዳዋለ የሚያሳይ በኦዲተር ወይም በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

3) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ በግል እጩዎች ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 21. <u>በቁሳቁስ ስለሚሰጥ የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ</u>**

መንግስት በዚህ መመሪያ መሰረት በቁሳቁስ የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በተጠቃሚው ፍላጎት መሠረት ፖስተር፣ ቲ-ሸርት፣ ኮፍያ፣ ቢልቦርድ፣ ባነር፣ የእጩ ምልክት፣ የእጩ ፎቶግራፍ፣ ኮምፒዩተር፣ ፕሪንተር፣ ፎቶ ኮፒ ማንሻ፣ ፋክስ፣ ወይም ስካነር፣ በራሪ ጽሁፍ፣ ማይክሮፎን፣ ባጅ፣ ስቲከር፣ ባንዲራና የመሳሰሉትን እንደ ሁኔታው ገዝቶ ወይም አሳትሞ ማከፋፈልን ያካትታል።

**አንቀጽ 22. <u>በአገልግሎት መልክ ስለሚሰጥ የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ</u>**

1. መንግስት በአገልግሎት መልክ የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በመንግስት የመሰብሰቢያ አዳራሽ በነፃ እንዲገለገሉ ማድረግ፣ በህግ መሠረት የመገናኛ ብዙኃን አገልግሎት መስጠት፣ ወይም የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ያለክፍያ እንዲያገኙ ማድረግን ያካትታል።

2. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁ አንቀጽ 77 መሠረት፡-

ሀ/ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ በሚገኘው ገቢ ላይ ምንም ዓይነት የገቢ ግብር
አይከፍልም።

ለ/ ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በህግ በተወሰነ መሰረት የገቢ ግብር ሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ከማድረግ ነጻ ነው።

3. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ በዚህ መመሪያ መሠረት ከተመደበለት የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ለመገናኛ ብዙሃን መጠቀሚያ የተሰጠውን ድርሻ ቦርዱ በገንዘብ አስልቶ ለሚመለከተው የፖለቲካ ፓርቲ ያሳውቃል።

**አንቀጽ 23.** **<u>ከመንግሥት ስለሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄ አቀራረብ</u>**

1. ለፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግስት የሚሰጠው ዓመታዊ የገንዘብ ድጋፍ በሁለት ጊዜ ክፍያ ይፈጸማል፡፡

2. የፖለቲካ ፓርቲዎች በአዋጁ አንቀጽ 100(2) እና በዚህ መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ የሚሰጣቸው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ተሰልቶ እንዲሰጣቸው ከመስከረም 30 ቀን በፊት ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረገውን ድጋፍ መጠን እሰከ ነሃሴ 30 ቀን ድረስ ይወስናል፡፡

3. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት የፖለቲካ ፓርቲው በሚያቀርበው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሚገባውን የገንዘብ መጠን ይሰጣል፡፡ ሆኖም በበጀት ዓመቱ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ የፖለቲካ ፓርቲ ገንዘቡን ከመስጠቱ በፊት ቦርዱ ፓርቲው በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት በመንግሥት የተሰጠን የገንዘብ ድጋፍ የሂሳብ መዝገብ አስቀርቦ በመመርመር ማጽደቅ ይኖርበታል፡፡ ቦርዱ ፓርቲው የሂሳብ መዝገብ ምርመራ ሪፖርት የሚያቀርብበትን ጊዜ በአንድ ወር ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 24.** **<u>በመንግስት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ አስተዳደር</u>**

የፖለቲካ ፓርቲው የመንግሥት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ከሚያደርጉት መስፈርቶች ውስጥ ሲያጓድል፤

ሀ) ለመስፈርቱ የተቀመጠውን ድጋፍ ያጣል፣

ለ) መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ መጠቀም አይችልም፤

ሐ) መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

መ) በዚህ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት ተመላሽ የሚያደርገውን ገንዘብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ወደ ቦርዱ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

ሠ) በዚህ አንቀጽ በፊደል ተራ (ለ) እና (ሐ) የተደነገጉት ቢኖሩም የፖለቲካ ፓርቲው የተሰጠውን ድጋፍ ሥራ ላይ ለማዋል መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን አስቀድሞ የገባቸው የውል ግዴታዎች ካሉ ቦርዱ ተመላሽ መደረግ ከሚገባው ገንዘብ ታሳቢ ሊያደርግለት ይችላል፡፡

**አንቀጽ 25.** **<u>ስለተጠያቂነት እና ቅጣት</u>**

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ ከታለመለት ዓላማ ውጭ ካዋለ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ ወይም ሐሰተኛ የሂሳብ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣ ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር በተያያዘ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሀ) የሚሰጠው ድጋፍ ሊቀነስበት ወይም ሊቋረጥበት ይችላል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተመለከተውን ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ህግ በአዋጁ የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል።

2. ቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲ አላግባብ ወጪ የሆነን ገንዘብ ክስ በመመስረት ወይም በማቻቻል ሊያሰመልስ ይችላል።

3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫ ዘመን ምርጫ እንቅስቃሴ ጀምሮ ሳይጠናቀቅ አቋርጦ የወጣ እንደሆነ ለምርጫው ሂደት ማስፈጸሚያ በቁሳቁስና በቋሚ ንብረት የተሰጠውን የመንግሥት ድጋፍ እንዲመልስ ሊደረግ ይችላል።

**አንቀጽ 26. <u>ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሚቀርብ የሂሳብ ሪፖርት</u>**

1. ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተደረገውን ድጋፍ አስመልክቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ ሪፖርቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል። ሪፖርቱ የሚከተሉትን የያዘ ይሆናል፤

ሀ) በበጀት ዓመቱ ለፓርቲዎች ድጋፍ እንዲውል በመንግሥት የተመደበውንና ከሌላ ምንጭ የተገኘውን ጠቅላላ የገንዘብ መጠን፣

ለ) በበጀት ዓመቱ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የተመደበውን የድጋፍ መጠን፣

ሐ) ህግ በሚፈቅደው መሠረት በእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በበጀት ዓመቱ ወጪ የተደረገ የገንዘብ መጠን፣

መ) በበጀት ዓመቱ የታየውን የሂሳብ ሚዛን።

2. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ የተመለከተውን ሪፖርት ለዋናው ኦዲተርም ይልካል።

**አንቀጽ 27. <u>ለ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ በመንግስት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ስለሚከፋፈልበት የጊዜ ሰሌዳ</u>**

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 እና 24 የተደነገጉት ቢኖሩም ቦርዱ **ለ6ኛው** ጠቅላላ ምርጫ ከመንግስት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሚያደርግ መመዘኛን የሚያሟላ የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት አስፈላጊውን መመዘኛ ማሟላቱን የሚያመለክት ዝርዝር መረጃ ለቦርዱ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ በወጣ በ15 ቀናት ውስጥ ያቀርባል። በዚሁ መሰረት፤

ሀ) ማንኛውም ለፖለቲካ ፓርቲ በቁሳቁስ የሚሰጥ የመንግስት ድጋፍ የእጩ ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ፣ በጥሬ ገንዘብ የሚሰጠው ድጋፍ ደግሞ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይከፋፈላል።

ለ) ማንኛውም ለፖለቲካ ፓርቲ በአገልግሎት መልክ የሚሰጥ ድጋፍ ቦርዱ ባወጣው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የምርጫ ዘመቻ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ዕለት ድረስ ይሰጣል።

**አንቀጽ 28. <u>ስለፌዴራል ዋና ኦዲተር ኃላፊነት</u>**

1. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከመንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና ለግል እጩዎች የተሰጠን ማንኛውንም የፋይናንስ ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ በራሱ ተነሳሽነት ወይም አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ በማንኛውም ጊዜ ለመመርመር ይችላል።

2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር በዚህ አንቀጽ መሠረት የመረመረውን የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ አጠቃቀም ሪፖርት ከአስፈላጊው መግለጫ ጋር ለቦርዱ ያቀርባል።

## ምዕራፍ ሶስት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 29. <u>የጊዜ ሰሌዳ ስለማሻሻል</u>**

ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው አዋጁን መሰረት በማድረግ ከመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ የሚከፋፈልበትን የጊዜ ሰሌዳ ሊያሻሽል ይችላል። የተሻሻለውን የጊዜ ሰሌዳ የመንግስትን የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል እጩዎች እንዲያውቁት ያደርጋል።

**አንቀጽ 30. <u>ስለተጠያቂነት</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር የአዋጁን ወይም የዚህን መመሪያ ድንጋጌ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። በአግባቡ ተግባራዊ ካላደረገ በአዋጁ፣ በዚህ መመሪያ ወይም በሌላ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

**አንቀጽ 31. <u>ስለ ቅጣት</u>**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግስት የሚሰጠውን የፋይናንስ ድጋፍ ከታለመለት ህጋዊ አላማና ተግባር ውጪ ካዋለ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ ወይም የሀሰት የሂሳብ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር የተያያዘ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ በአዋጁና በወንጀል ሕጉ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

**አንቀጽ 32. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከመጋቢት 16 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርቱካን ሚዴቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ